# የሽቱትጋርት የአውሮፓ የስፖርትና ባህል ዝግጅት
# **2018** ምን ይመስላል**?**

በማለዳ ተነስቼ ሰውነቴን በመታጠብ፣ ጢሜን በማስተካከል፣ ጥርሶቼን ከፋቅሁ በኋላ ቡና ለማፍላትና ቁርስ ለማዘጋጀት መንጎዳጎድ ቀጠልኩ።የቡና ማፍያ ውሃ ቀድቼ በማፍያው ጨምሬ ቡና በማንኪያ ለክቼ በማጣሪያ ወረቀቱ ላይ ካደረግሁ በኋላ ዘግቼ ኮረንቲውን በመጫን አስነሳሁት። በመክተፊያ ላይ ትልቅ ዳቦ አጋድሜ በልኩ ሁለት ቁራሾች በቢላ በመቁረጥ አዘጋጀሁ።

በተቆረጡት ሁለት የዳቦ ቁራጮች ላይ ዛዝኪ የሚባል ነጭ ሽንኩርት ያለበት ቀባሁ።በተጨማሪ ዩጎርት በተልባ፣ በተፈጨ ቀረፋና ኩርኩማ ጨምሬ ካማሰልኩ በኋላ አንድ ብርጭቆ ውሃ የሚጠጣ ቀድቼ አስቀመጥኩ። ቡናው ከፈላ በኋላ አንድ ስኒ ቡና ቀዳሁ።አሁን የቁርስ ሰዓት በመሆኑ ቁርሴን እየበላሁ ቡናውን እየጠጣሁ ካጣጣምኩ በኋላ የቀዳሁትን የብርጭቆ ውሃ ጠጣሁ።የቁርስ ወቅቱ በዚህ መልክ ተጠናቀቀ። ግን ምራቃችሁ ቢመጣ እኔ ተጠያቂ አልሆንም። ለሽቱትጋርት ጉዞ አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ ሻንጣ አዘጋጅቼ ስለነበረ፣ በመጀመሪያ ትልቁ ውስጥ መግባት ያለባቸውን እቃዎች ካስገባሁ በኋላ ቁልፉን ቆልፌ ይዞ ለመሄድ እንዲመች አድርጌ አዘጋጅቼ ተውኩት።ከዚያም ትንሹ ሻንጣ ውስጥ የጉዞ ትኬት የሚጠጡና የሚበሉ ፈራፍሬዎች የሚነበቡ ነገሮች ፣ ካሜራ ጨምሬ ካዘጋጀሁ በኋላ፣ ትልቁ ሻንጣ ላይ አስቀመጥኩት። ከቤት ከቀኑ አምስት ሰዓት ከአስር ደቂቃ ሁለቱንም ሻንጣዎች ይዤ የከተማ አውቶቡስ የሚቆምበት ስፍራ በመጓዝ፣ ከቀኑ አምስት ሰዓት ከሃያ ሁለት ደቂቃ የሚመጣውን አውቶቡስ ይዤ ለአስር ደቂቃ ከተጓዝኩ በኋላ፣ ወርጄ የከተማ የመሬት ውስጥ ባቡር ይዤ ለ 15 ደቂቃ ከተጓዝኩ በኋል ወርጄ ሌላ የከተማ ባቡር ቀይሬ ወደዋናው የከተማው ዋና ባቡር ጣቢይ ተጓዝኩኝ። ከዋናው የከተማው የባቡር ጣቢያ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ከሃምሳ ስምንት ደቂቃ ይዤ ጉዞዬን ወደሽቱትጋርት ዋና የባቡር ጣቢያ አመራሁ።

የ16ኛው የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን የስፖርትና ባህላዊ ዝግጅት በሽቱትጋርት የእግር ኳስ ቡድን አዘጋጅነት በቫይሊንገን ከተማ የተዘጋጀ እንደሆነ ተገልጿል።ለዚህም ቀደም ብዬ በቫይሊንገን ከተማ ለአምስት ቀን ሆቴል በመያዝ በየቀኑ 2.50 ኢሮ በመክፈል በአውቶቡስ እስከ ሩንድስፖርትሃለን ድረስ በመጓዝ ወደ ዝግጅቱ ቦታ ለመድረስ ችዬአለሁ። ማክስኞ እለት በቫይሊንገን ከተማ ወዳለው የዝግጅቱ ቦታ በማምራት የፌዴሬሽኑን የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተወካዮች በዝግጅቱ ስፍራ ተገኘተው እየተመካከሩ ነበር። በዚህን ወቅት አንድ መርዶ ከአዘጋጁ አገር እንደተነገራቸውና ሁኔታው እንዳበሳጫቸው ሹክ አሉን።የአጨዋች ዳኞች ጉዳይ ነበር።አዘጋጁ የሽቱትጋርት ቡድን ለፌዴሬሽኑ ቴክኒክ ኮሚቴ ተወካይ 16 የጀርመን አጨዋች ዳኞችን ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን እንዳረጋገጠለት ነበር።

የቴክኒክ ኮሚቴው ተወካይ ደግሞ 6 ኢትዮጵያውያን አጨዋች ዳኞችን እንዳዘጋጀ ለፌዴሬሽኑ የሰራ አስኪያጅ ኮሚቴ አረጋግጦ ነበር። ማክሰኞ እለት ግን በተጨባጭ የቀረቡት የጀርመን አጨዋች ዳኞች ቁጥር 6 መሆኑና የኢትዮጵያውያን አጨዋች ዳኞች አንድም እንዳልተገኘ ነበር። ይህ ዱብ እዳ ለፌዴሬሽኑ በጣም ከባድ ነበር። በማግስቱ ረቡዕ እለት ሁለት የጀርመን አጨዋች ዳኞች ተጨምረው 8 ሆነዋል።ከኢትዮጵያውያን ወገን አንድ አጨዋች ዳኛ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ኢትዮጵያዊ ተገኝቶ ነበር። እሱ አብሮ ቢደመር 9 አጨዋች ዳኞች ነበሩ። ነበር።ኢትዮጵያዊው አጨዋች ዳኛ ባቀረበው ጥቆማ መሰረት ዘጠኝ አጨዋች ዳኞች ስለነበሩ፣ በሶስት ሜዳዎች ላይ እያንዳንዱ ጨዋታ ከዚህ በፊት እንደሚደረገው በአንድ ዋና አጨዋች ዳኛና በሁለት ረዳት ዳኞች እንዲመራ ሃሳብ አቅርቦ ነበር።ይህን አስተሳሰብ ወይም ጥቆማ ቀርቶ በአንድ አጨዋች ዳኛ ብቻ ያለረዳት ዳኞች እንዲመራ አጨዋች ዳኞቹም የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊም ፍላጎት ነበር።ኢትዮጵያዊው አጨዋች ዳኛ ያቀረበው ሃሳብ ውድቅ ተደርጎ እያንዳንዱ ጨዋታ በአንድ

አጨዋች ዳኛ ብቻ እንዲመራ የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ ወስኖ ተግባራዊ ተደርጓል።በዚህም ምክንያት ከተሳታፊ ቡድኖች በኩልም ከፍተኛ ተቃውሞ ነበር። ረቡዕ እለት ጨዋታዎች በአንዳንድ አጨዋች ዳኛ በአራቱ ሜዳዎች ላይ እንዲካሄዱ በማድረግ በየሜዳዎቹም ታዛቢዎች እንዲኖሩ ተደርጎ እንዲሰራ ተደርጎ ነበር። በመሃሉ በተወሰኑት ሜዳዎች ያለታዛቢዎች በኋላም በሁሉም ሜዳዎች ያለታዛቢዎች እንዲካሄድ ተደርጓል።

ይህም የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ የማቀናጀት ፍላጎት በጣም ተቀያያሪ ነበር።በዚህም ምክንያት የታዛቢዎች መኖር በአብዛኛው ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል።በመጀመሪያው ቀን የቢጫ፣ የቢጫና ቀይ እንዲሁም የቀይ ካርዶች፣ የጎል አግቢ ሪፖርቶች በተገቢው መንገድ አልተመዘገቡም። የፌዴሬሽኑ ኮምፒዩተር ላይ የሚመዘግበው አቶ ጳውሎስ መመዝገብ የሚችለው የጨዋታውን ውጤቶች ብቻ በመሆኑ፣ ካርዶችንና ጎል አግቢዎችን መመዝገብ የሚያስችል ፕሮግራም የለውም። በዚህም ምክንያት አንድ በአቶ ክንፈ የተዘጋጀ የመመዝገቢያ ፎርም ተባዝቶ፣ አቶ በላይ እንዲመዘግብ ተድርጎ ነበር።አቶ በላይም በሚገባ ከአጨዋች ዳኞች የጨዋታ ውጤቶችን፣ ጎል አግቢዎችን፣ ቢጫ፣ ቢጫና ቀይ እንዲሁም ቀይ ካርዶች በመቀበል በመመዝገብ ተግባራዊ አድርጓል። ረቡዕ ማታ የቡድኖች ተወካዮችና የፌዴሬሽኑ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት የሚገኙበት አንድ ስብሰባ ተደርጎ ነበር።

የሚገርመው ነገር የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ በዋናነት ተገኝቶ ለተከሰቱት ችግሮች አብሮ መፍትሄዎችን መሻት ሲገባው፣ ጭራሽ ይባስ ብሎ በዚህ ስብሰባ ላይ አልተገኘም ነበር። በስብሰባው ላይ የተገኙት የየቡድኖቹ ተወካዮች አጨዋች ዳኞችን በሚመለከት ከየቡድኑ ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦችን በማቀናጀት፣ በታዛቢነትና በረዳት ዳኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች ተጠይቆ ወደ አምስት ሰዎች ብቻ ተገኝተዋል።ለዚህም አቶ ክንፈን ሃላፊነቱን ወስዶ እንዲያቀናጅ ተወስኖ ነበር። ሐሙስ እለት አቶ ክንፈ አንድ የተዘጋጀ ፎርም ለውጤት፣ ላካርዶችና ጎል አግቢዎች አባዝቶ በማቅረብ አቶ በላይ ከዳኞቹ ውጤቱን፣ ጎል አግቢዎችና ካርዶችን በመመዝገብ ሃላፊነቱን በሚገባ ተውጥቷል።የአንደኛ ድቪዚዮን የተሞሉ ፎርሞችን የቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊው ወስዶ ዬት እንዳደረሰው ባለመታወቁ፣ አቶ በላይ ተበሳጭቶ ነበር።

የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ በስብሰባው ላይ መገኘት ሲገባ ሳይገኝ ቀርቶ ሐሙስ በጠዋት መጥቶ ረቡዕ ማታ በቡድን ተወካዮች የተወሰነውን ውሳኔ በመሻር እሱ በፈለገው መንገድ ፕሮግራሙን አካሂዷል።ይህም ችግር መፍጠሩ አልቀረም። ጨዋታዎች ያለ ረዳት ዳኞች መካሄዳቸው ቀጥሏል።ታዛቢዎች መታዘባቸውን በአብዛኛው ተግባራዊ አላደረጉም። ከጨዋታ ሜዳ አንወጣም! በኢትዮ - ሽቱትጋርትና በኢትዮ- ሆላንድ ቡድኖች መሃከል በሜዳ ቁጥር አንድ ላይ የተካሄደው ኢ-ስፖርታዊ ድርጊት፣ የብዙዎቹ የሁለቱ ቡድኖች ተጨዋቾች ኳስ መጫወት ትተው ወደ ቦክስ ውድድር በመቀየር እርስ በእርሳቸው ተደባድበዋል።ይህም መረን የለቀቀ ከእግር ኳስ ጨዋታ ጋር የማይጣጣም የተደባዳቢዎች ስርዓት አልበኝነት የታየበት ነበር።አጨዋቹ ዳኛም ጨዋታውን በድብድቡ ምክንያት አቋርጧል።በኋላም ሁለቱ ቡድኖች በፈጸሙት ኢ- ስፖርታዊ ድርጊቶች ተጸጽተው በመጨባበጥ ይቅር ተባብለዋል።ይቅር መባባሉ ጥሩም ቢሆን የድብድቡ ድርጊት ግን መወገዝ ያለበት ነው።

በቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ ይህንን ጨዋታ አስመልክቶ፣ ምን ዓይነት ውሳኔ እንደተወሰነ አይታወቅም። የኢትዮ - ስዊዲን ቡድን ከጨዋታ ሜዳ አንወጣም ብሎ በኋላ በስንት መከራ በልመና ከጨዋታ ሜዳ እንዲወጣ ተደርጓል።ይህ በጣም ጸያፍና በምንም መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ የስርዓተ አልበኝነት ድርጊት በመሆኑ የሚወገዝ ድርጊት ነው። የኢትዮ- ስዊዲን ቡድን ጨዋታ ሜዳ ውስጥ ገብቶ በሜዳ ሁለት ላይ ጨዋታ እየተካሄደ አልወጣም ማለቱ፣ ኢ-ስፖርታዊና ስርዓት አልበኝነቱን ያረጋገጠበትና ሊወገዝ የሚገባው ድርጊት ነው።መጀመሪያም ሌላ ሜዳ ላይ ገብቶ አልወጣም ማለቱም በተጨማሪ ተጠቅሷል።የፈለገ ዓይነት ስህተት ቢሰራ ይህንን ዓይነቱን ድርጊት መፈጸሙ እራሱን ከሕግ በላይ በማድረግ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ያጣ ድርጊት ነው። ለዚህም ተጨዋቾቹና የቡድኑ አሰልጣኝና መሪዎች በእኩል ደረጃ የሚወገዙ ናቸው።በመጨረሻም በስንት ልመና የኢትዮ- ስዊዲን ቡድን ከሜዳው ወጥቶ ጨዋታው እንዲቀጥል ተደርጓል።
ዓርብ እለት ደግሞ ኢትዮ- በርገን የሚባለው ቡድን ከኖርዌይ፣ ጨዋታ ሜዳ ቁጥር አንድ ውስጥ ገብቶ ከሜዳው እልወጣም በማለት፣ በሜዳው ላይ ጨዋታ እንዳይካሄድ አድርጓል።ይህም ድርጊት ኢ-ስፖርታዊና ስርዓት የለሽ ድርጊት ሲሆን፣ መወገዝ

ያለበት ድርጊት ነው። ከሁለት ሰዓት በላይ ሜዳውን አልለቅም በማለታቸው ቢለመኑም አሻፈረኝ አሉ። ከዚያም ፖሊስ መጥራት ግድ ሆነ።ፖሊስ ከመጣ በኋላም የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ ከፖሊሶቹ ጋር ውይይት መክፈቱ ትክክል አልነበረም።ማድረግ የነበረበት የኢትዮ- በርገንን ቡድን ፖሊሶቹ ከሜዳው እንዲያስወጡለት ማድረግ ነበር።በመጨረሻም የኢትዮ- በርገን ቡድን ሜዳውን ሳይለቅ በእለቱ ሊደረግ የሚገባቸው ጨዋታዎች ለሚቀጥለው ቀን እንዲዛወሩ ተድርጓል።

የኢትዮ- በርገን ቡድን ይህን ውሳኔ ሲሰማ ራሱን እንደ አሸናፊ በመቁጠር በጭብጨባ ተቀብሎታል።ይህንን ቡድንና የቡድን ሃላፊዎች ላይ ፌዴሬሽኑ ምን እርምጃ እንደሚወስድ ገና አልታወቀም። የልጆችና የወጣቶች እግር ኳስ ውድድር ህጻናትና ታዳጊ ወጣቶች ከምዝገባ እስከ መጨረሻው ውድድር ድረስ እቶ ፋሲል ሃላፊነቱን በሚገባ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ጥሩ ስራ ስርቷል።ለዚህም ሊመሰገን ይገባል።አንድ ሊሻሻል የሚገባው ነገር ለወጣቶቹም አጨዋቾች ዳኞች ሊዘጋጅላቸው የሚችልበትን ሁኔታ ለወደፊቱ ቢታሰብበት መልካም ነው። የኢትዮ- በርገንና ኢትዮ ለንደን ጉዳይ ሁለቱ ቡድኖች በአንደኛ ዲቪዚዮን፣ በአንድ ግሩፕ ውስጥ ቅድመ ማጣሪያ ውድድሮችን አካሂደዋል።ሁለቱም ቡድኖች አራት አራት ጨዋታዎች አካሂደው፣ ኢትዮ- በርገን ሁለት ጨዋታዎችን በማሸነፍ አንድ ጨዋታ እኩል ለእኩል ሲወጣ፣ አንድ ጨዋታ ተሸንፏል።

ኢትዮ- ለንደንም ሁለት ጨዋታዎችን በማሸነፍ አንድ ጨዋታ እኩል ለእኩል ሲወጣ፣አንድ ጨዋታ ተሸንፏል።ስለሆነም ኢትዮ- በርገን ሰባት ነጥብ ሲኖረው ኢትዮ- ለንደንም ሰባት ነጥብ አለው።ይህም ማለት ሁለቱም ቡድኖች በነጥብ እኩል ናቸው። የሚቀጥለው በጎል ብልጫ ያለውን ቡድን ከሁለቱ ቡድኖች መፈለግ ነው።የኢትዮ- በርገን ያገባው ጎል ብዛት ስድስት ሲሆን፣ የገባበት ጎል ብዛት ደግሞ አራት ነው።ካገባው ጎል የገባበት ሲቀነስ(6-4) ሁለት ጎል ይኖረዋል።የኢትዮ- ለንደን ቡድን ያገባው ጎል ብዛት ስድስት ሲሆን፣ የገባበት ጎል ብዛ ደግሞ እራት ነው።ካገባው ጎል የገባበትን ጎል ሲቀነስ (6-4) ሁለት ጎል ይኖረዋል።ይህም ማለት የኢትዮ- በርገንና የኢትዮ- ለንደን ቡድኖች በነጥብም በጎልም እኩል ናቸው።በዚህ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ የአንድ ግሩፕ ሁለት ቡድኖች የፊፋ ሕግ ባስቀመጠው መዳኛ መሰረት፣ ሁለቱ ቡድኖች እርስ በእርሳቸው በግሩፑ ውስጥ ሲጫወቱ ያሸነፈው ቡድን እንዲያልፍ የሚያደርግ ነው።

በዚህም መሰረት ኢትዮ - ለንደን ከኢትዮ - በርገን ጋር በግሩፑ ውስጥ ተጫወተው፣ ኢትዮ- ለንደን ሁለት ለባዶ ኢትዮ - በርገንን አሸንፏል። በዚህም ምክንያት ኢትዮ - ለንደን ለሚቀጥለው የጥሎ ማለፍ ውድድር ያልፋል።በዓለም ዋንጫ በምሳሌነት ጃፓንና ሴኔጋል በግሩፓቸው ተጫውተው፣ ጃፓን ሴኔጋልን በማሸነፉ ለሚቀጥለው ማጣሪያ ውድድር እንዲያልፍ መደረጉን መጥቀስ ጠቃሚ ይሆናል። ለጥሎ ማለፍ ውድድር ያለፉ ቡድኖች ከአንደኛ ዲቪዚዮን ስምንት ቡድኖች ከአራቱ ግሩፖች አንደኛና ሁለተኛ የሆኑት ሲያልፉ፣ ከሁለተኛ ዲቢዚዮን አራት ቡድኖች ከሁለቱ ግሩፖች አንደኛና ሁለተኛ የሆኑት አልፈዋል። በዚህ መሰረት ኢትዮ ኮሎኝ አንደኛ፣ ኢትዮ - ኖርዌይ ሁለተኛ፣ ኢትዮ- ዘበርሊን አንደኛ፣ ኢትዮ- አበበ ቢቂላ ሁለተኛ፣ ኢትዮ- ሲዊዝ አንደኛ ኢትዮ ለንደን ሁለተኛ፣ ኢትዮ - ካታንጋ አንደኛ ኢትዮ ሆላንድ ሁለተኛ ከአንደኛ ዲቪዚዮን ወደ ጥሎ ማለፍ ሲያልፉ፣ ከሁለተኛ ዲቪዚዮን ኢትዮ- ትሮንድሃይም አንደኛ ኢትዮ - ፍራንስ ሁለተኛ፣ ኢትዮ - ዴንማርክ አንደኛ፣ ኢትዮ - ቡና ሁለተኛ ሆነው አልፈዋል። ለመጨረሻ የዋንጫ ውድድር ከአንደኛ ዲቪዚዮን ኢትዮ - ለንደንና ኢትዮ - ሆላንድ ሲያልፉ፣ ከሁለተኛ ድቪዚዮን ደግሞ ኢትዮ - ፍራንስና ኢትዮ - ቡና አልፈዋል። የዋንጫው ባለቤት ለመሆን በማሸነፍ ያረጋገጡት፣ ከአንደና ዲቪዚዮን ኢትዮ ለንደን ሲሆን፣ ከሁለተኛ ዲቪዚዮን ደግሞ ኢትዮ - ፍራንስ ነው።

ሁለቱንም ቡድኖች እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እንሻለን። አንድ ጥያቄ ይኖረናል። ይኸውም የቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊው እንዴት ነው ኢትዮ-ኮሎኝን ከኢትዮ - ለንደን እንዲሁም ኢትዮ - ሆላንድ ከኢትዮ - ኖርዌይ ጋር እንዲጋጠሙ ያደረገው? ያለምንም መረጃዎች የተሰጡ ሽልማቶች ለኮኮብ ግብ ጠባቂ፣ ኮኮብ ተጨዋቾች እንዲሁም ለጠባይ ተብሎ የተሰጠው ሽልማት ያለምንም መረጃ ወይም ክትትል በመሆኑ፣ ፈጽሞ ትክክል አይደለም።ቴክኒክ ኮሚቴው ያደረገው ምንም የክትትል ስራ አልነበረም።ይህ ለወደፊቱ ተሻሽሎ በትክክለኛው መንገድ ሊሰራ የሚገባው ነው።

የመጨረሻው የዋንጫ ጨዋታ እየተካሄደ ይደረግ የነበረው ቃለ መጠይቅና ተጨማሪ ስለ ሙዚቃ ዝግጅት በድምጽ ማጉሊያ ይደረግ የነበረው ሂደት መታረም አለበት።ጨዋታ እየተካሄደ የዚህ ዓይነቱን ድርጊት ማካሄዱ ተገቢ አይመስለንም።ሌላው

ተናጋሪው ጋዜጠኛ ለቡና ቡድን ያለውን ወገንተኛነት ለማሳየት፣ የኢትዮ- ፍራንስ ቡድንን ስም ለመለወጥ ይዳዳው ነበር።ይህም „የኢትዮ- ፍራንስ-ቡና‟ በማለት ነበር። ጥሩ አይመስለንም። ምክንያቱም ስም መለወጥ ይሆናል።ቡናን የመደገፍ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ትንሽ በተለይ እንደ ጋዜጠኛ ጠንቀቅ ማለቱ ጠቃሚ ይመስለናል። የጽዳት ሰራተኞች በበቂ አለማዘጋጀት የኢትዮ - ሽቱትጋርት አዘጋጅ ቡድን በጣም በሚያሳፍር ሁኔታ ሚዳዎቹ ላይ የሚጣሉ ቆሻሻዎች፣ ከተጣሉ በኋላ ተከታትሎ የሚያነሱና የሚያጸዱ በቂ ሰዎች አላዘጋጀም።ሌላው በየቦታው ቆሻሻ መጣያ ትላልቅ ላስቲኮችን በብዛት በየቦታው ማስቀመጥ ሲገባው፣ ይህን አላደረገም።በአጠቃላይ ለጽዳቱ ስራ በቂ ዝግጅት አላደረገም። በዚህ ነጥብ የዴንሃግ ዝግጅት በጥሩ ምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ምግብና መጠጥ አገልግሎቶች የምግብ ድንኳኖች እስከዛሬ ፌዴሬሽኑም አስር የምግብ ድንኳኖች እንዲሆኑ ሲፈቅድ፣ ባሁኑ ወቅት ግን ከአስር የሚበልጡ የምግብ ድንኳኖች መኖራቸው ተጠቅሷል።

ለነጋዴዎቹ እንዳሰቡት የመሸጥ ሁኔታ እንዳልነበረ ይነገራል። ይህም ገንዘብ ለመሰብሰብ ካልሆነ፣ አዘጋጁ አገር ለምን ቁጥሩን መጨመር እንዳስፈለገው ግልጽ አይደለም። የምግብ ድንኳኖችን የመጠጥ አገልግሎት በጣም መራራቃቸው በጣም ተተችቷል።ቢቻል ለወደፊቱ ምግብ፣ ቡናና መጠጥ አንድ አካባቢ እንዲሆን ቢደረግ የተሻለ መሆኑን የሚቀጥለው አዘጋጅ አገር ቢያስብበትና ቢያስተካክለው መልካም ነው። የመጠጥ ትኬት በየቀኑ መለወጡን ለህዝቡ በተደጋጋሚ መንገሩ ቅንነት የተላበሰ ይሆናል።የመጀመሪያው ቀን የተገዙ የቢራ ትኬቶች ለሚቀጥለው ቀን እንዳይሰራ መደረጉ ፈጽሞ ህዝብን በማዘናጋት ለመዝረፍ ነው። የመጠጡን ትኬት በየቀኑ ቀለሙን ለመቀየር ከተፈለገ፣ ቀደም ብሎ የተገዛውን ትኬት በቀኑ ትኬት መለወጥ እንዲቻል ማድረግ ነው። ይህ ድርጊት በሁለተኛው ቀን ያደረ ትኬት ይለወጥ ነበር።
በኋላ ግን መለወጥ አይቻልም ተብሏል። ይህ አሰራር ለህዝብሙ በደንብ መገለጽና መነገር አለበት። የሚጠጣ ውሃ ለተጨዋቾች ለእያንዳንዱ ቡድን ተጨዋቾች ጋዝ የሌለው የሚጠጣ ውሃ አዘጋጁ አገር የተወሰነውን ማቅረብ እለበት። ይህም በተሟላ መልኩ በአዘጋጁ በሽቱትጋርት አልተሟላም።በኋላም ጋዝ ያለበት የተወሰነ ውሃ ለተጨዋቾች ቀርቦ ቡድኖቹ ቅሬታቸውን አሰምተዋል።ፌዴሬሽኑ በራሱ ወጪ ጋዝ የሌለው ውሃ በመግዛት ለቡድኖች ለማከፋፈል ጥረት አድርጓል።ይሄ ጥሩ ነው። በፌስቡክ በፌዴረሽኙ ስም የተሰራጩ መረጃዎች ችግር በግለሰብ ደረጃ በፌዴሬሽኑ ስም ሳይጣራ መረጃዎችን በማሰራጨት ለተለያዩ ችግሮች መከሰት ምክንያት ሆኗል።በፌስቡክ ምንም ዓይነት መረጃዎች ባይሰራጩ የተሻለ ነው። በውድድሩ ወቅት ሁልግዜ አንድ ከአጨዋች ዳኞች ውጤቶችን የሚቀበልና የሚመዘግብ፣ ከዚያ ወደ ኮምፒዩተር የሚያስገባ ሰው ተመድቦ መስራት አለበት።

ለቡድኖች የሜሰጡ መረጃዎች ካሉ በቡድን ተወካዮች ብቻ ማድረጉ የተሻለ ይሆናል። የእግር ኳስ ውድድር መመሪያ ደንብ እያንዳንዱ ቡድን የእግር ኳስ ውድድር መመሪያ ደንቡ ተልኮለት የተቀበለ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል። በተጨባጭ ግን ብዙዎቹ የመመሪያ ደንቦች በተግባር ላይ አልዋሉም።ለምሳሌ ቁጥር 6፣ 8፣ 14፣ 19 ና 23 ን መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል።ሌላው አንድ ጨዋታ በአንድ የመሃል አጨዋች ዳኛና ሁለት ረዳት ዳኞች መካሄድ እንዳለበት ሲሆን፣ የቅድመ ማጣሪያ ውድድሮች በሙሉ ያለ ረዳት ዳኞች ተካሂደዋል።

ማንኛውም ቡድን የቴክኒክ ክፍሉን ማነጋገር የሚችለው በቡድኑ አሰልጣኝ ወይም አምበል ወይም የቡድን ሃላፊ ሲሆን የተደረገው ግን ብዙ ተጨዋቾች በአንድ ግዜ በመምጣት ነበር። የስፖርታዊ ጨዋነት ተሸላሚ የሚሆነው ቡድን በጠቅላላ ውድድሩ ወቅት ቡድኑ ከአጨዋች ዳኞች በሚያገኘው ቢጫ፣ ቢጫና ቀይ እንዲሁም ቀይ ካርድ ብዛት ተደምረው ነው።ይህም በቴክኒክ ኮሚቴው በኩል ተፈጻሚነት አላገኘም። የቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊው የብቸኛነት አሰራር የቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊ የነበረው ግለሰብ ከሌሎች ጋር ተባብሮና ተመካክሮ ለመስራት ፍላጎት እንደሌለው የታየበት ነበር።የአጨዋች ዳኞች ችግር የተከሰተው ስለ አጨዋች ዳኞች እምብዛም ትኩረት ባለመስጠቱ በተጨባጭ የተሰራ ነገር አልነበረም።በቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊው ስድስት ኢትዮጵያውያን አጨዋች ዳኞችና አሰራ ስድስት የጀርመን አጨዋች ዳኞች ለውድድሩ እንደሚቀርቡ የተነገረው እውነት አለመሆኑ ነው።

ምክንያቱም የተገኙት ስምንት አጨዋች ዳኞች ብቻ ነበሩ።ዘጠነኛ አንድ ኢትዮጵያዊ አጨዋች ዳኛ ተጨምሮ በሶስት ሜዳዎች ሶስት ጨዋታዎች በረዳት ዳኞች ማካሄድ ይቻል ነበር። ግን የቴክኒክ ኮሚቴው ሃላፊ ይህንን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ አልፈለገም

ነበር።ለምን ለሚለው መልሱን እሱ ብቻ የሚያውቀው ይሆናል።ሌላው በአንደኛ ዲቪዚዮን ውስጥ የጥሎ ማለፍ ውድድሩ ያለምንም የተዘጋጀ ፕሮግራም የተካሄደ ነበር።

ከተንሳይት በቃና

ኦገስት 8 ቀን 2018 ዓ.ም.